# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር—
መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቀደም፡፡

ቁጥር 33 ቀን 6/4/ 68

## የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዋና ቅራኔ

የየካቲት 1966 የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰፊ ሪቮሉሽናዊ እንቅስቃሴና ከዚያም ወዲህ የተፈጠረው ሁኔታ ሁሉ በማያሻማ አኳኋን ያረጋገጠው አንድ ነገር አለ፡፡ይኸውም፣ የሃይለስላሴ ፊውዶ-ፋሽስት መንግስት ማንም ሊገምተው ከቻለው በላይ የበሰበሰ እንደነበረና፣ በዚያውም መጠን ደግሞ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች የፖለቲካ ንቃት፣ የድርጅት ስፋት፣ በጠቅላላ አነጋገርም ህሊናዊው ሁኔታ ገና ያልተሟላ እንደነበረ ነው፡፡ከበሰበሰነቱም የተነሳ፣ ያልተደራጀው የንኡስ ከበርቴው ልዩ ልዩ ክፍል፡ሰራተኛውና ገበሬው በድንገት ሲነሳበት፣ የቀድሞ የጭቆናው መሳሪያ የነበረው ሰራዊቱና ፖሊሱ ሳይቀር በርሱው ላይ ዞርበት ገፍተር ሲያደርገው ፍርከስከሱ ወጣ፡፡የኢትዮጵያ ህዝብ የፖለቲካ ንቃት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለነበር ደግሞ፣ ይህ ሰፊ ህዝብ ተደራጅቶና እንደአንድ ሰው ሆኖ ተነስቶ፣ የመንግስትን ስልጣን ነጥቆ ሊወስድ አልቻለም፡፡

ከስርአቱ ብስብስነት የተነሳ፣ የገዥ መደቦች የህብረተሰብ መመርከዣ የነበሩት የገጠሩ ዝቅተኛ ጉልተኛ መደብ፣ አቀባባዩና የቢሮ ከበርቴው፣ ኢምፔሪያሊዝምም እራሱ ቢሆን፣ ወዲያውኑ ተያይዘው ተነስተው የሃይለስላሴን መንግስት ከውድቀት ሊያድኑት አልቻሉም፡፡እነዚህ ማንሰራራት የጀመሩት አሁን በቅርቡ ነው፡፡በሌላ በኩል ደግሞ ያገሪቱዋ ጠቅላላ ህሊናዊ ሁኔታ የቀረቀዘ ስለነበርም፣ ጭቁን መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎችም ወዲያውኑ ተደራጅተውና ተያይዘው፣ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን በተቀናበረ ትግል ለመደምሰስ ሊነሱ አልቻሉም፡፡እነዚህም በመጠኑ መደራጀት የጀመሩት አሁን በቅርቡ ነው፡፡

የሃይለስላሴ መንግስት በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ የፈፀመው አንዱ ትልቅ ወንጀል አገሪቱዋን በድንቁርና ጨለማ ውስጥ አፍኖ ማቆየቱ ነበር፡፡ህዝቡ በምንም አይነት ስለአለም ህዝቦች ትግልና ግስጋሴ እንዳያውቅ፣ እንዳይማር፣ እንዳይደራጅና በሪቮሉሽናዊ አስተሳሰብ ነቅቶ እንዳይነሳበት ያልፈፀመው በደል የለም፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የተደራጀና የነፃ መልክ የነበረው እንቅስቃሴ ቢኖር የኤርትራው ትግልና የተማሪው ያገር ውስጥና የውጭ አገር እንቅስቃሴ ነበር፡፡የነዚህም ሃይሎች ሪቮሉሽናዊ ንቃት እራሱ ውሱን እንደነበር ዛሬ በግልጽ ይታያል፡፡የኤርትራ ተዋጊዎች ከአስራ አራት አመታት በላይ የመሳሪያ ትግል ቢያደርጉም፣ የኤርትራን ሰፊ ህዝብ ትግል አቀናብሮ የሚመራ፣ ኢንተርናሽናሊስት አቋም ያለው ሪቮሉሽናዊ የወዝአደር ፓርቲ ለመፍጠር ይኸው እስከዛሬ አልቻሉም፡፡ከነዚያ ሁሉ የትልቅ መስዋእትነትና የተጋድሎ አመታት በሁዋላ፣ ዛሬ ገና በ1968 የኤርትራ ተዋጊዎች የግራ ክንፎች ''አንድ ሪቮሉሽናዊ ፓርቲ'' አስፈላጊ መሆኑን ማሳየት ጀምረዋል፡፡የተማሪውም የውስጥና የውጭ እንቅስቃሴ ብዙ መስዋእትነትን ካደረገ በሁዋላ፣ ዛሬ በጠቅላላው ሲታይ በትልቅ ውዥንብር ውስጥ ወድቀአል፡፡ደግሞም አሁን በኢትዮጵያ ብቅ ብቅ ያሉት የግራ ቡድኖች ከተማሪው እንቅስቃሴ የመነጩ ስለሆነ ውዥንብሩንም ብዙዎቹ የወረሱት ይመስላል፡፡

በኢትዮጵያ መቼውንም ቢሆን ግልጽ የሆነ የፖለቲካ ትግል ልምድ አልነበረም፡፡በቀድሞው ስርአት፣ ጠቅላላው የግራ ወገንም ሪቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ከዳር እስከዳር ይዞት የነበረው በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ላይ ነበር፡፡ያኔ ዋነኞቹን ጠላቶች መለየት ምንም ያህል አስቸጋሪ ነገር አልነበረም፡፡በየካቲት እንቅስቃሴ ሳቢያ ፊውዳሊዝም ቢያንስ በመንግስት ስልጣን ደረጃ ከተገረሰሰ ወዲያና ኢምፔሪያሊዝምም ቢያንስ በቃላት ደረጃ መደፈር ከጀመረ ወዲያ፣ ያገሪቱዋ የሃይሎች አሰላለፍ በሌላ መልክ ቀርቦአል፡፡ስለዚህም ወዳጅንና ጠላትን እንደቀድሞው በቀላሉ ለመለየት የማይቻልበት ሁኔታ አለ፡፡ይህንን ሁኔታ በደንብ ሊያጣራ ይችል የነበረው የሙሉ ዲሞክራሲያዊ መብት መኖር

ነበር::ግን ከደርጉ ፀረዲሞክራሲያዊነት የተነሳ፣ በትግል፡በግልጽ የፖለቲካ ክርክር ማን ከማን
ጋር እንደተሰለፈ ለማሳየት አልተቻለም::ይህም ለውዥንበር ነዣዎችና ለአድሃሪዎች አመች ሆነ::

ማንኛውም ሪቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ሊያድግና ግቡን ሊመታ የሚችለው ከታወቁትና ከለየላቸው
አድሃሪዎች ጋር በሚያደርገው ተጋድሎ ብቻ ሳይሆን፣ በሪቮሉሽኑ ደጋፊነት ቀርበው ነገር ግን የሪ
ቮሉሽኑ አደናቃፊ የሆኑትን፣ በግራው ወገን ውስጥ ያሉትንና ሰርገው የሚገቡትን የቀኝና ''የግራ''
አድርባዮችንም ጭምር በሰፊው ህዝብ ፊት ለማጋለጥ ሲችል ነው::

አንዳንድ ተራማጆች የዚህ አይነቱን ዲሞክራሲያዊ ክርክር ይፈሩታል፤ የግራውን ሃይል፣
ተራማጁን የህብረተሰብ ክፍል ይከፋፍላል ይላሉ::እነዚህን ተራማጆች የምንመክራቸው የሪቮሉሽናዊችን
ታሪክ እንዲያስታውሱና በዚሁ በአዲስ አበባ ውስጥም በመካሄድ ላይ ያሉትን አንዳንድ የቀበሌ
የወጣቶች ማህበራት ስብሰባዎችን ሄደው እንዲጎበኙ ነው::ሃቀኛ ክርክር ለትግላችን የግድ አስ
ፈላጊ ነው::ሃቀኛ ክርክር ብዙ ትምህርት ይሰጣል፣ የተሳሳቱትን መስመሮች ያጋልጣል፣መስመርን
ያጠራል::ያለፖለቲካ ትግል የፖለቲካ መስመር ጥራት አይገኝም::እንደዚህ አይነቱን ትግል እውነተኛ
አብዮታውያን አይፈሩትም::ዲሞክራሲያዊ ትግል ለአብዮታውያን ዋና መሳሪያቸው ነው::እውነተኛ አብ
ዮታውያን ዲሞክራሲያዊ ክርክርን በስም ማጥፋት፣ ባሉባልታና በሌላ ሌላ የፊውዳል ኢንተሪግ ሊተኩት
አይሹም::ዲሞክራሲያዊ ክርክር አድሃሪዎችን፣ ግራመሰል አወናባጆችንና ውዥንበር ነዣዎችን ለብቻ
ነጥሎ ያወጣቸዋል፤ ጠቅላላውን እንቅስቃሴም አጠናክሮ ያወጣዋል::ይህንን ዲሞክራሲያዊ አረማመድ
የማይወዱ የጠቅላላውን እንቅስቃሴ መጠናከር የማይወዱ፣ የሰፊውን ህዝብ የተጠናከረ ሃይል የሚፈሩ
ፀረህዝብ ክፍሎች አለያም ሪቮሉሽናዊ ድልን ከሪቮሉሽናዊ ትግል ነጥለው የሚያዩ የዋህ ተራማጆች
ናቸው::

ለዚህ አይነቱ የፖለቲካ መስመር ማጣሪያ ትግል ጊዜው አሁን ደርሶአል::ስለዚህም በአ
ሁኑ ሰአት በኢትዮጵያ ግራ ውስጥ የልዩነት ነጥብ የሆኑ አንዳንድ ነገሮችን እዚህ ላይ ለማንሳት
እንፈልጋለን::የኢትዮጵያ የጊዜው ሪቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ወዳጆችና ጠላቶች የትኞቹ መደቦችና ሃይ
ሎች ናቸው? ባገራችን ሁኔታ ዛሬ ያንደኛ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ቅራኔዎች የትኞቹ ናቸው? የደ
ርጉ የመደብ ባህርይ ምንድነው? የመንግስትን ስልጣን ሰፊው ህዝብ እንዴት አድርጉ ይይዛል?

እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን የሰፊው ህዝብ ድምጽም ዲሞክራሲያም ደጋግመው አንስተዋል::
ከፍ ብለው በተነሱት ጥያቄዎች ላይ ትንተና ስና ቀርብ የምንጠቅመው በተለይ ባለፉት ሁለት የዲሞ
ክራሲያ ቁጥሮች በ22 እና በ23 ነው::እዚህ ላይ ለማሳየት የምንፈልገው ይህ ጋዜጣ ያለውን
ውዥንበር፣ ፀረሪቮሉሽናዊ አስተያየትና የፖለቲካ መስመር ነው::በዚህ መስመር ብዙ ሀቀኛ ተራማ
ጆች ተወናብደዋል::አሁን እንግዲህ መንቃት አለባቸው እንላለን::

የጋዜጣው ቁጥር 23 ''ፊውዳሎች፣ ኢምፔሪያሊስቶችና ፋሽስቶች አንድም ሶስትም ናቸው''
በሚል፣ እራሱ አወናባጅና አደንቋሪ በሆነው ''የስላሴዎች ምስጢር'' በመሰለ አርእስት ስር
ሰፋ ያለ ''ትንተና'' አቅርቦአል::የዚህ ጽሁፍ ጠቅላላ ይዘት ፊውዳሎች —እነመንገሻ ስዩም፣
ነጋ ተገኝ፣ አሊ ሚራህ፣ ወዘተ.— ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና ''ፋሽስቶች'' ማለትም የደርጉ
''ምርጥ መኮንኖች'' የተያያዙ ስለሆኑ፣ ሶስቱንም ጠላቶች የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድነት መዋጋት
አለበት የሚል ነው::ይህንን ቁጥር ያነበበ ማንም ሃቀኛ ሪቮሉሽናዊ ስለዲሞክራሲያ ሰዎች ሊስተው
የማይችል አንድ እውነት ይኖረዋል::ሰዎቹ ወይ አውቀው ለማወናበድ ታጥቀው የተነሱ ናቸው፣ ወይንም
የጊዜውን ሁኔታ፣ ያገሪተዋን የመደቦች አሰላለፍ፣ የህብረተሰቡን ቅራኔዎች አዝማሚያ፣ ከዚህም
የተነሳ የኢትዮጵያ ግራ መከተል ያለበትን መስመር ፈጽሞ አልተረዱትም ማለት ነው::

ይህ የጋዜጣቸው ቁጥር በሁለተኛ ገፁ ላይ የአብዮቱን ወዳጆችና ጠላቶች በመደብና በህብ
ረተሰብ ክፍል በሞላ ጉደል ደህና አድርጉ ይደረድራል::በተለይ የአብዮቱ ጠላቶች ''ጉልተኞች፣
የተለያዩ ከበርቴዎች... አለም ቀአፍ ኢምፔሪያሊዝም''፣ የአብዮቱ ባለቤትና ወዳጅ ደግሞ ከዘ
ጠና በመቶው በላይ የኢትዮጵያን ህዝብ የሚያጠቃልል መሆኑን ከገለፀ በሂላ፣ የሚከተለውን ያሰፍ
ራል:—

> ''ዋናው ቅራኔና ትግል የሚገኘው በነዚህ ሁለት ቡድኖች መካከል ሲሆን አብዮቱ ወደፊት በሚጊዘበት ወቅት ተፈጥሮ ባጭር ጊዜ ውስጥ <u>የጎላው</u> አዲስ ቅራኔ በሰፊው ህዝብና በምርጥ መኳንንቶች መንግስት መካከል ያለው ነው::....''/ሰርዝ የተጨመረ/

ከዚያም፣ ዴሞክራሲያ ከቀድሞውም እንዴት ''ሳይንሳዊ'' ትንተና ሲያቀርብ እንደነበር እራሱን ያወድስና ጽሁፉ:-

> ''ፋሽስቶች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በተለያዩ መንገዶች የተሳሰሩ፣ በጠላትነትም ደረጃ ይበልጥ ጎልተው ወይም ኮስሰው ሳይሆን ባንድነት መታየት ያለባቸው መሆኑን አያሌ ጊዜ ጠቅሶአል''
> ይላል::

''ባጭር ጊዜ ውስጥ <u>የጎላው</u> አዲስ ቅራኔ'' ምን ማለት ነው? ''በጠላትነትም ደረጃ ይበልጥ <u>ጎልተው ወይም ከስሰው ሳይሆን ባንድነት</u> መታየት አለባቸው'' ማለትስ? ይህ የመጨረሻው አረፍተ ነገር፣ ፊውዳሊስቶችም:ኢምፔሪያሊዝምም:''ፋሽስቶችም'' እኩል ጠላቶች ናቸው ማለቱ ከሆነ በመጀመሪያው ጥቅስ ''ዋናው ቅራኔና ትግል'' በፊውዳሊዝም—ኢምፔሪያሊዝምና በሰፊው ህዝብ መካከል ነው የሚለውን እንደሚቃረን ግልጽ ነው::ደግሞም፣ ''የጎላው አዲስ ቅራኔ'' የሚለው፣ ምንም ያህል ትርጉሙ ያልተጣራ የቃላት ውርወራ፣ በሰፊው ህዝብና በደርጉ መካከል ያለው ቅራኔ ዋናው፣ የመጀመሪያው ደረጃ ቅራኔ ሆኖአል ማለት አይደለም ወይ? ይህ ከሆነ ደግሞ ባንድ ህብረተሰብ ውስጥ ባንድ በተሰጠ ጊዜ ሁለት <u>ዋና ቅራኔዎች</u> ሊኖሩ ይችላሉ ለማለት ታስቦ ይሆን?

ይህ ሁሉ የተምታታ አቀራረብ መቼስ የነዚህን ተራማጆች የትንተና ድህነት ከማጋለጡ በስተቀር፣ ባንድ በኩል በፊውዳሊዝም—ኢምፔሪያሊዝምና በሰፊው ህዝብ መካከል፣ በሌላው በኩል ደግሞ በሰፊው ህዝብና በደርጉ መካከል ያሉት ቅራኔዎች ምን አይነት ባህርዮች እንዳሉአቸው ቀንጣት ያህል ለአንባቢ አያስረዳም::እንዲያውም አንባቢው የሚይዝ የሚለቀውን እንዲያጣው የሚያደርግ የተምታታ አነጋገር ነው::

ከላይ እንደተጠቀሰውና መላ ጽሁፉ እንደሚያሳየው የዚህ የዴሞክራሲያ ቁጥር ዋና አላማ የኢትዮጵያ ህዝቦች ሶስቱንም ጠላቶች ባንድነት መዋጋት እንዳለባቸው ለማሳየት ነው::ግን እነርሱ እንደሚሉት ደርግ በርግጥ ''ፋሽስት'' ከሆነ ለምን ከነመንገሻ ስዩም ጋር ፀረፋሽስት ግንባር አናቋቁምም? ሌላው ቀርቶ ከኢምፔሪያሊዝም ከራሱ ጋር ወዳጅነትን ፈጥረን ለምን ደርጉን አንገለብጠውም? በስታሊን ስትመራ የነበረችው ታላቋ ሶቭየት ህብረት ለማይቀረው ጦርነት ፋታ ለማግኘትና ለመዘጋጀት መጀመሪያ ላይ ከፋሽስቱ ሂትለር ጋር የወዳጅነት ውል ፈርማ፣ ከዚያም ጦርነቱ ከተጀመረ ወዲያ ከቀንደኞቹ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋር በፋሽስቶች ላይ የአንድነት ግንባር አልፈጠረችምን? ጀግናው የቪየትናም ህዝብ በፈረንሳይ ቀኝ ገዥዎች ላይ በከፊልም ቢሆን <u>ከራሱ ፊውዳሊስቶች ጋር</u>፣ በጃፓን ፋሽዝም ላይ ደግሞ ከፈረንሳይ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ያንድነት ግንባሮች ፈጥሮ አልተዋጋምን?

የዴሞክራሲያን የመሰለ አቋም ያላቸው ''የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን''/የኢዙና ፌዴሬሽን/ መሪዎች ይህንን ''ደርግ ፋሽስት!'' የሚለውን ቀዝታቸውን ማሳመን ሲያቅታቸውና ከነመንገሻ ስዩም ጋር በገሃድ መሰለፋቸው ሲታይባቸው፣ ''የኢትዮጵያ ፋሽዝም የቀድሞው አይነት ፋሽዝም ስላልሆነ ፀረፋሽስት ግንባር መፍጠር አያስፈልግም'' የሚል ስንኩል ፈሊጥ ለማጭበርበሪያ ፈጥረዋል::የዴሞክራሲያም ሰዎች እንደዚያው ማድረግ ሊኖርባቸው ነው::

ዴሞክራሲያ ቁጥር 23 በስደት ያሉት ጉልተኞችና ባገር ውስጥ ያሉት የመደብ ወንድሞቻቸው ''እየተወያዩ እየተደራጁ በሃሳብ ሃይላቸውን የሚያስተባብሩ የአንድ የጋራ የትግል ግንባር አባላት ወደመሆኑ እያመሩ ነው::የተከታዮቻቸው ቁጥር፣ በተለይ ከሶስት ወራት ወዲህ፣ ባፋጣኝ እያደገ ነው''ይላል::ቀጥሎም እነመንገሻ ስዩም በሳውዲ አረቢያ ተሰብስበው እንደነበርና እነዚህ አድሃሪዎች ''የጀመሩት ቀልድ አለመሆኑን'' በደንብ ይጠቁማል::በጣም ጥሩ ትንተና ነው::/በነገራችን ላይ፣ እነዚሁ አድሃሪዎች እኤአ መስከረም 7 ቀን 1975 ላይ በጄዳ ከIኤልኤፍ መሪ ከኦስማን ባላህ ባቤ ጋር ''ግንባር'' ለመፍጠር መደለታቸውንና የኤርትራ ግንባር ''በትግራይና በአውሳ ላሉት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄዎች ሙሉ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ'' እንደሚሰጥ፣ እኤአ በጥቅምት 2 ቀን 1975 በመግለጫ ማስታወቁን ጽሁፉ አይጠቅስም::ጽሁፉ እንዴት ይህንን ተልቅ ቁምነገር

ሳተው?/ እንደዚሁም አለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም እነመንገሻ ስዩምንም ደርጉንም እንደሚረዳ ጽሁፉ ያመለክታል::ይህንን ለመጠቆም የተሰነዘረው የጽሁፉ ክፍልም እንደሌላው ሁሉ የተምታታ ነው:: ''ሰፊው ህዝብ ከኢምፔሪያሊስት ብዝበዛ ለመላቀቅ የሚያካሂደውን ታላቅ አብዮት ለማውደም አሜሪካ፣ ምእራብ ጀርመንና የተቀሩት ኢምፔሪያሊስት ሃገሮች ባለሁለት ራስ ጦር ወርውረዋል... ወዘተ.'' ይላል::ሊሆን ይችላል::ግን የዲሞክራሲያን አመራር የትንተና ደካማነት ወይንም የአውቆ ማወናበድ ስራ የሚያጋልጡ ሁለት እውነቶች አሉ::

አንደኛ:— ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና ሌሎችም ኢምፔሪያሊስቶች በመሳሪያ ሽያጭና በ''እርዳታ'' አማካይነት በወታደራዊው መንግስት ላይ ተጽእኖ አንዳላቸው ምንም ጥርጥር የለውም::ይሁንናም፣ በተለይ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ባሁኑ ሰአት አዝማሚያው ወዴት እንደሆነ ገና ካልለየለት፣ አደገኛ ሊሆንበት ከሚችልና ቢያንስ በታላቅ ደረጃ ፀረኢምፔሪያሊስት ከሆነው ደርግ እነመንገሻ ስዩምን እንደሚመርጥ ሳይታለም የተፈታ ነው::ለዚህ ትንሽ ማስረጃ ከተፈለገ የኢምፔሪያሊስት አገሮችን ጠቅላላ ኘረስ ብቻ በደንብ መመልከት ይበቃል::

ከነዚህ አንዱን ቀንደኛ የሆነውን ለመጥቀስ ያህል ብቻ፣ የኦክቶበር 21፣ ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ዋና አፈቀላጤ የሆነው ''ዘ ኒውዮርክ ታይምስ'' የተባለው ጋዜጣ ''በኢትዮጵያ መንግስቱ የሚገዛው በአመጽ ነው፤ ጠቅላላ ዑዥንበር —ኬኦስ— ነግሶአል'' በሚል አርእስት ወታደራዊውን መንግስት በማጥላላትና እነመንገሻ ስዩምን፣ የሃይለስላሴንም የቀደሞ ስርአት ጭምር በማሞገስ ጽፍአል::የጽሁፉ ይዘት ''ፋሽዝም'' በኢትዮጵያ ነግሶአል ከሚለው የዲሞክራሲያ አቋምና ከነመንገሻ ስዩም ቋንቋ በምንም አይለይም::በዚህ ደረጃ፣ ሶስቱም የደርግ ጠላቶች በተጨባጭ አኳኋን ባንድነት ተሰልፈዋል::ዲሞክራሲያ እነመንገሻ ስዩምን በማጋለጡ፣ ያውም በተድበሰበሰ ሁኔታ፣ ከነርሱና ከኢምፔሪያሊዝም ደጋፊነት አመለጠ ለማለት አይቻልም::

በተረፈም ደርጉ በወሰዳቸው አንዳንድ ፀረኢምፔሪያሊስት እርምጃዎችና —''መሬት ላራሹም'' እራሱ በባህርዩ ፀረኢምፔሪያሊስት ነው!— በደርጉ አመጣጥ፣ በመደብ ይዘቱ፣ እነመንገሻ ስዩም፣ ነጋ ተገኝ፣ አሊ ሚራህ ይበልጥ ለኢምፔሪያሊዝም የሚያመቹ መሆናቸውን ማንም ሪቮሉሽናዊ በቀላሉ ሊረዳ ይችላል::ደግሞም ወደፊት በግልጽ ኢምፔሪያሊዝም ከነዚያ ጋር ተሰልፎ እንደሚመጣ ማየታችን ፈጽሞ አይቀርም::

በደርጉ ውስጥና ውጭም የተጀመረው ትግል እየተፋፋመ ሄዶ ትክክለኛ መስመር የሚያዝበት፣ ፊውዳሊዝም:ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ሙሉ በሙሉ የሚመቱበት፣ ሰፊው ህዝብም ተደራጅቶና ታጥቆ ስልጣንን ለወጉ ሳይሆን በእርግጥ በእጁ የሚያስገባበትና የሚጠብቅበት ሁኔታ ላይ ካልተደረሰ በስተቀር የኢምፔሪያሊዝም አደጋ ያለ ነው::ኢምፔሪያሊዝም ባመቸው መሳሪያ ይጠቀማል፤ ብዙ አማራጭ መሳሪያዎችም አሉት::የተራማጆች አንዱም ተግባር በመሃል የሚዋልሉ ክፍሎችን ገፍትሮ ወደኢምፔሪያሊዝም ጉያ መጣመር ሳይሆን ወደህዝቡ ሰፈር ሊደባለቁ የሚችሉትን መሳብ፣ ሊሳቡ የማይችሉትንም በተቻለ መጠን መነጣጠልና ከነሙሉ ትጥቃቸው ወደጠላት ሰፈር እንዳይገቡ መከላከል ነው::አንዱን ህብረተሰባዊ ቡድን /ስልጣን ኮርቻ ላይ ወጣም አልወጣ/ እና ወደህዝቡ ሰፈር፣ ወደአብዮቱ ልንስበው የምንሞክረውን ያህል ኢምፔሪያሊዝምም ወደራሱ ሰፈር፣ ወደፀረአብዮት ሊስበው ይፍጨረጨራል::ይህ እራሱ አንድ ትግል ነው::ግራና ቀኝ ዘላይና የቅራኔዎች ክምችት የሆነውን እንደደርግ ያለውን አካል ቢቻልም እያንዳንዱን የደርግ አባል ሚናውን እንዲለይ፣ ስልፉን እንዲያሳምር፣ ወደ አብዮቱ እንዲደባለቅ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መፍጠር አለብን::ይህም በመሰረቱ የአብዮቱን ደጋፊዎች ማብዛት ነው::ይህ መቼም ለዲሞክራሲያ ምስጢረ—ስላሴን ለማፋለስ መሞከር ነው፤ የከፋ ሃጢአት ነው::

ሁለተኛ:— ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ፣ ዲሞክራሲያ ከፍ ብሎ ''ዋናው ቅራኔና ትግል'' በፊውዳሊዝም—ኢምፔሪያሊዝምና በሰፊው ህዝብ መካከል ያለው መሆኑን፣ ነገሩ በተምታታ አኳኋን ቢቀርብም፣ ተናግሮአል::እዚህም ላይ፣ እነመንገሻ ስዩም—ነጋ ተገኝ ''ለቀልዱ'' ያልተነሱ መሆናቸውንና ''ከደንከል በረሃ እስከመተማ፣ ከተከዜ እስከአባይ ያለው የአድሃሪያን ትግል መቀነባበሩ እንደማይቀር'' ገልጾአል::/በነገራችን ላይ፣ ለምን ''ከተከዜ'' ብቻ? ለምንስ እስከ''አባይ''

ብቻ?/ ይህ ቢምታቷና ከሂሳው አንድ ግልጽ ያልሆነ ነገር ቢኖርበትም በመሰረቱ ትክክለኛ ትንተና ነው::ግን ከዚህ ትንተና መከተል የነበረበት መደምደሚያ ፊውዳሊዝም—ኢምፔሪያሊዝም፣ ወይንም እነመንገሻ ስዩምና ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም፣ አሁንም የኢትዮጵያ ህዝቦች ዋና ጠላቶች ናቸውና በቅድሚያ በነርሱ ላይ መተባበር አለብን የሚል መሆን ነበረበት::ባንድ በኩል እነመንገሻ ስዩም—ነጋ ተገኝ እየተጠናከሩ መጥተዋል እያለና፣ አመጣጣቸውም ደርጉን አስወግደው ስልጣንን ለመያዝ መሆኑን እየጠቆመ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ''ፋሽስቱ'' ደርግና ደመኛ ጠላቶቹ እነመንገሻ አንድ ናቸውና በሰፊው ህዝብ ላይ ህብረት ሊመሰርቱ የሚችሉ ማስመሰል በሬ ወለደን ለማሳመን መሞከር ብቻ ሳይሆን ሰፊው ህዝብ የጊዜውን ወዳጆችና ጠላቶች በትክክል እንዳይለይ በማወናበድ በቀጥታ ጠላቶቹን ማገዝ ነው::

ዲሞክራሲያ ቀጥር 23፣ እና እስከምናውቀው ድረስ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ከኢትዮጵያ ድንበር ውጭ ያለውን የሃይሎች አሰላለፍ ለማጤን ሞክሮአል::በተለይ አድሃሪ የአረብ መንግስታት እነአሊ ሚራህን፣ መንገሻ ስዩምን፣ ወዘተ. እንደሚረዱ ጠቅሶአል::በጣም ጥሩና የሚያስመሰግን አቀራረብ ነው::ግን እነዚሁ አድሃሪ ሃይሎች የኤርትራንም ግንባሮች ከሃይለስላሴ ጊዜም ይበልጥ ዛሬ በገፍ እንደሚረዱ አይጠቅስም::ለምን? ከዚህም አልፎ፣ ''እነዚህ ሁሉ/አድሃሪ ያካባቢው አገሮች መንግስታት/ የምርጦቹን መንግስት ጠልተው አይደለም፣ በዚህ ረገድ አቋማቸው ከኢምፔሪያሊዝም አይለይም ...ወዘተ.'' የሚል ፈጽሞ የተወናበደ አስተሳሰብ ያቀርባል::አድሃሪ የአረብና ያካባቢው አገሮች የደርጉን አዝማሚያ የማይጠሉ ከሆነና አብዮቱን እንደሚያጨናግፍላቸው ካወቁ ለምን ካሁኑ ለነአሊ ሚራህ የሚሰጡትን ሚልዮን ለርሱ አይሰጡትም? ገና ለመንግስት ስልጣን ከሚታገሉት ከነመንገሻ ስዩም—ነጋ ተገኝ—አሊ ሚራህ፣ ቀድሞ ስልጣኑን የያዘው ሃይል አይሻላቸውም ነበርን? ይህም የዲሞክራሲያ ሌላ የትንተና ጉድለትና አወናባጅ አቋም ነው::

ዲሞክራሲያ ቀጥር 23 እጅግ የሚያሳዝን፣ የወንድሞቻችንን የትንተና ደካማነት ወይንም አንዳንዶቹ አውቀው ለማወናበድ መነሳታቸውን የሚያሳይ ጽሁፍ ነው::አልፎ አልፎ ደህና አድርገው ሁኔታውን ያዩትና በንኡስ ከበርቴው ድንፋታ ብቻ ተመልሶ አይናቸው የሚታወር ይመስለባቸዋል::

ያገሪቱን የመደቦችና የሃይሎች አሰላለፍ በሚመለከተው በኩል የኛ አቋም ግልጽ ነው:: በፊውዳሊዝም—ኢምፔሪያሊዝምና በሰፊው ህዝብ መካከል ያለው ቅራኔ አሁንም ዋነኛው ነው::ባገሪቱ ላይ ያንዣበበው ትልቅ አደጋ የነመንገሻ ስዩም—አሊ ሚራህና ሌሎችም ፊውዳሊስቶች በኢምፔሪያሊዝም ተደግፎ ፀረሬቮሉሽኑን ከሁሉም አቅጣጫ ማምጣት ነው:: የፊውዳሊዝም—ኢምፔሪያሊዝም የቀድሞ መመርኮዛዎች፣ ቢሮክራሲያዊውና አቀባባይ ከበርቴው፣ በደርጉ ውስጥ ያሉትም አድሃሪዎች ጭምር፣ በዚህ አይነቱ ፀረሬቮሉሽናዊ ቀለበሳ ሊተባበሩ የሚችሉ፣ አሁንም ቢሆን በብዙ ገመዶች ከነዚያ ጋር የተሳሰሩ ሃይሎች ናቸው:: የኤርትራ ግንባሮች አድሃሪ መሪዎችም ወደዱም ጠሉም ከነዚህ አድሃሪ ሃይሎች ጋር ተሰልፈዋል:: የአረብና የሌሎችም አድሃሪ ያካባቢ አገሮች ሁኔታም እንደዚያው ነው::ሁሉም በኢትዮጵያ የተያዘውን ሬቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ርቆ ሳይሄድ ሊያቆሙት እንደሚፈልጉ ለማንም ሃቀኛ ተመልካች ግልጽ ነው::ይህንን እንቅስቃሴ ለመስበርም የሚመቸው የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ ያመራሩን ቦታ የያዘውን ደርግ በመገልበጥም እንደሆነ እንደዚሁ ግልጽ ነው::

ይሁንናም፣ በዚህ ደርግና በሰፊው ህዝብ መካከል ቅራኔ የለም ማለት አይደለም::ደርጉ እስከዛሬ ፀረዲሞክራቲክ ሃይል ሆኖ ሰፊው ህዝብ በቶሎ እንዳይነቃ፣ እንዳይደራጅና ለማይቀረው ፀረፊውዳል—ፀረኢምፔሪያሊስት—ፀረቢሮ ከበርቴ የመጨረሻ ጦርነት እንዳይዘጋጅ አድርጉአል::ፍፁም አሰቃቂ የሆኑ ፋሽስታዊ እርምጃዎችንም በየጊዜው ወስዶአል::በየከተማው በወዛደሮች ላይና በየገጠሩም በለፍቶአዳሪው ገበሬ ላይ የተወሰዱት ፍፁም ፋሽስታዊ የሆኑት የጭፍጨፋ እርምጃዎች ከታጋዩ ሰፊ ህዝብ አእምሮ በቀላሉ የማይፋቁ ቋሚ ምስክሮች ናቸው::/በነገራችን ላይ ግን ''ፋሽስታዊ እርምጃዎችን'' መውሰድና ፋሽስታዊ ስርአትን ማቋቋም ሁለት ልዩ ነገሮች መሆናቸውን እናስታውስ/

በሌላ በኩል ግን መሰረታዊ ነገሮችን የሚነኩ ተራማጅ እርምጃዎች አሉ::አድሃርያንን ባንድነት ያሰለፉአቸው እነዚህ እርምጃዎች ናቸው:: የእነዚህም እውነተኛ አድሃርያን፣ ግንባር ቀደም የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች መነሳት በደርጉና በሰፊው ህዝብ መካከል ሊኖር ይችል የነበረውን የመጀመሪያ

ደረጃ ቅራኔ ወደሁለተኛ ደረጃ ቅራኔ አዛውርታል፡፡ስለዚህም ወደድንም ጠላንም፣ በንኡስ ከበርቴ አለሁ—አለሁ—ባይነት ካልተመራንና ተጨባጩን ሁኔታ ለማየት አንፈልግም ካላልን በስተቀር፣ እንደዲሞክራሲያዎች፣ እነመንግሽም፣ ኢምፔሪያሊዝምም፣ ደርጉም አንድ ናቸውና ስስተንም እኩል እንዋጋቸው አንልም፡፡የተራማጆች ተግባር ጊዜያዊ ወዳጆችን ሁሉ ባንድነት ማስተባበርና በዋናው ጠላት ላይ መረባረብ፣ በርሱ ላይ ብቻ ማተኮርና በርሱ ላይ ሊሰለፍ የሚችለውን ሁሉ ሃይል ማሰለፍ መሆኑን የሪቮሉሽኖች ተያሪና ታሪክ ያስተምረናል፡፡ወዳጅንና ጠላትን፣ ጊዜያዊም ሆነ ዘላቂ፣ አማትቶ ሁሉም ያው ነውና ውጋው፣ ወይንም ለትወጋው ትችላለህ ማለት ሰፊውን ህዝብ በተጨባጭ መንገድ ለጠላቶቹ አሳልፍ መስጠት ነው፡፡ተራማጆች ስለደርጉ ሊኖራቸው የሚገባቸው አቋም አብዮታዊ ሂስ የሚለው የኛ አቋም ብቻ ነው የምንለውም ለዚህ ነው፡፡''

''አብዮታዊ ሂስ'' ስንል ምን ማለታችን ነው? ዋናው መነሻችን የመንግስት ስልጣን በሚያስተማምን አኳኋን ወደሰፊው ህዝብ እጅ የሚገባበትን መንገድ መሻት ነው፡፡ለዚህም እስከመጨረሻው እንታገላለን፡፡ስለዚህም ይህን ደርግ በፀረህዝብነቱ፣ በፀረዲሞክራሲያዊነቱና በፀረአብዮትነቱ እንቃወመዋለን፣ እንታገለዋለን፡፡ሰፊው ህዝብ ተደራጅቶና ታጥቆ ከደርጉም ሆነ እርሱን ከሚተካው ሌላ ተመሳሳይ መንግስት እጅ ስልጣንን ፈልቅቆ እንዲወስድ የሚያስችለውን ትምህርት እንዲያገኝ፣ እንዲደራጅ አስፈላጊውን ትግል እናደርጋለን፡፡ዋናው አብዮታዊ ቁምነገር የአብዮቱ ወደፊት መግፋት፣ ስልጣን ወደተደራጀ ሰፊ ህዝብ እጅ መግባትስለሆነ ግንባር ቀደሙና ሃቀኛው ተራማጅ በጠቅላላውም ሰፊው ህዝብ እየታገለ እንዲደራጅ፣ እየተደራጀም እንዲታገል እንታገላለን እንጂ ያለምንም ዝግጅት በስልጣን ዝውውር ላይ ብቻ በማተኮር በጓዳ ሾለከው ለሚገቡ ቀለባሾች፣ ለፀረአብዮት ሃይሎች መሳሪያ አንሆንም፤ ከሰፊው ህዝብ ዋና ጠላቶች ጋር አንተባበርም፡፡በአብዮቱ አንፃር እያየን ፀረአብዮት ሃይሎችን በየደረጃቸው እየለየን እንታገላቸዋለን፡፡የተለያዩ ጠላቶችን እንደየጠላትነት ደረጃቸው በተለያዩ ዘዴ እንመታቸዋለን እንጂ ሁለት እግር ስላለን ሁለት ዛፍ ላይ እወጣለሁ የሚለውን የታክቲክ ስህተት በማድረግ ሁለት ጦርነት በአንድ ጊዜ አናውጅም፡፡ለአብዮቱ መግፋት ስንል የሁለተኛ ደረጃ ጠላቶችን በልዩ ልዩ ዘዴ እናዳክማቸዋለን እንጂ ከዋናው ጠላት ጋር እንዲሰለፉ አናደርግም፤ ወይም ከዋነኛው ጠላት ጋር ተሰልፈን በሁለተኛ ደረጃ ጠላቶች ላይ አንዘምትም፡፡ የሂሳችን አብዮታዊነት ከሞላጐደል ይህ ነው፡፡

ወደልዩነት ነጥቦች እንመለስና፣ በዚህ ጽሁፍ መጀመሪያ ላይ ባነሳናቸው የልዩነት ነጥቦች ላይ ሰፋ ያለ አስተያየት ማቅረብ ባስፈለገ ነበር፡፡በብዙዎቹ ላይ ወደፊት 'የሰፊው ህዝብ ድምጽ' ይመለስባቸዋል፡፡አሁን ግን አንዲት የመጨረሻ ነጥብ፡— ዲሞክራሲያ ስለደርጉ የመደብ ባህርይ ደጋግሞ የተምታቱ አስተያየቶችን አቅርቦአል፡፡በጋዜጣው ቁጥር 22 የሚከተለው ሰፍሮአል፡—

> ''በደርጉ ውስጥ በደርግ ስም የመንግስት ስልጣን የያዙት ጥቂት መኮንኖች ለስልጣናቸው ሲሉ የቻሉትን ያህል ሰፊውን የኢትዮጵያ ህዝብ ከማፈንና ከመጨፍጨፍ የማይመለሱ፣ <u>ለቢሮ ከበርቴያቸና ለኢምፔሪያሊስቶች አገልግሎት ያደረ</u>፣ የስልጣናቸውን ጊዜ የሚያራዝም መስሎ ከታያቸው ከፊዳሊስቶችም ጋር ከመታረቅና አብሮ ከመስራት የማይመለሱና የወጣላቸው መሆናቸውን አሳይተዋል፡፡....'' /ሰርዝ የተጨመረ/

በቁጥር 23 ደግሞ፣ ይኸው ደርግ

> ''መንግስትነቱ ግን ለቢሮ ከበርቴ፣ አቀባባይ ከበርቴና ንኡስ ከበርቴው መደብ ነው፡፡...'' ይላል፡፡

ባሁኑ ጊዜ የመንግስትን ስልጣን የያዘው የትኛው የህብረተሰብ መደብ ነው የሚለውን ጥያቄ በማያሻማ አኳኋን ለመመለስ ዲሞክራሲያን የጨነቀው ይመስላል፡፡ወንድሞች፣ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት የንኡስ ከበርቴው መንግስት ነው፡፡''መንግስትነቱ <u>ለዚህ</u> ነው፣ <u>ለዚያ</u> ነው'' አይደለም፡፡ <u>የ</u>ንኡስ ከበርቴው መንግስት ነው፡፡

ይህ የንኡስ ከበርቴ መንግስት ገና አልተደላደለም፡፡ይሁንናም፣ በተለይ በቢሮ ከበርቴውና ባቀባባዩም ላይ አንድ አይነት ጊዜያዊ ስምባገነንነትን አስፍሮ እነዚህን መደቦች፣ በዲሞክራሲያ ቋንቋ፣''በአርጩሜ'' የሚያስራ መንግስት ነው፡፡ስለዚህም፣ በነርሱና በደርጉ መካከልም ቅራኔ አለ፡፡ስለዚህም፣ እንደኢምፔሪያሊዝም ሁሉ፣ እንደነመንግሽ ስም ሁሉ፣ እንደዲሞክራሲያም የቢሮ

ከበርቴውና አቀባባይ ከበርቴው ''ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስትን'' ይፈልጋሉ፡፡በተቻለ ፍጥነት የሲቪል መንግስት እንዲፈጠርላቸው ይፈልጋሉ፡፡ከዲሞክራሲያ ጋር የተሰለፉት ንኡስ ከበርቴያችና ሌሎችም የቀኝ ክንፍ ሃይሎች ይህንን የሚፈልጉት ደግሞ ደርጉ የያዘባቸውን የመንግስት ስልጣን ለመውሰድ አቋራጭና ጥሩ ''አጋጣሚ'' መሆኑን ስለሚያውቁት ነው፡፡ስለዚህም፣ በጠባጭ መንገድ ሲታይ፣ በዲሞክራሲያና በደርጉ መንግስት መካከል ያለው ጥል በንኡስ ከበርቴው መደብ ውስጥ የሚደረግ የስልጣን ትንንቅ ነው ለማለት እንችላለን፡፡የዲሞክራሲያም ሆነ የደርጉ ሺህ ጊዜ የሰፊውን ህዝብ ስም ማንሳት ማንንም ሊያሳስት አይገባም፡፡

በነገራችን ላይ፣ ይህንን የደርጉን የመደብ ባህርይ በሚመለከተው በኩል፣ እነዚሁ የዲሞክራሲያ ወንድሞች በ30/6/67፣ የመሬት አዋጁን ምክንያት በማድረግ ባወጡት ልዩ እትም የሚቀጥለውን አስፍረው ነበር፡፡—

> ''ከወዝአደረና ከገበሬው አብራክ የተገኙት ተራ ወታደሮችና የበታች ሹማምንት፣ እንዲሁም ጥቂት ተራማጅ መኮንኖች ይህንን ከፍተኛ ቀራጥነት የሚጠይቅ ታሪካዊ እርምጃ በመውሰድ ለመደብ ጓደኛቸው ለሰፊው ህዝብ ያላቸውን ጽኑ ታማኝነት በጠባጭ ማስረጃ በማሳየታቸው ...ወዘተ.'' /ስርዝ የጨመረ/

ከመሬት አዋጁ እስከዛሬ ባሉት ጥቂት ወራት ውስጥ ደርጉም፣ የዲሞክራሲያም ወንድሞች የመደብ ባህርያቸውን ለውጠው ይሆን? አይደለም፡፡ሁለቱም እንደዚያው እንደቀድሞው ናቸው፡፡ፍጥረታቸውን አልለወጡም፣ ሊለውጡም አይችሉም፡፡ሁለቱም የንኡስ ከበርቴው መደብ አባሎች እንደመሆናቸው መጠን፣ በሬቮሉሽንና በፀረሬቮሉሽን መካከል እንደወላወሉ ናቸው፡፡ይህ እንግዲህ ባጠቃላይ ስንመለከት ነው፡፡ቀረብ ብለን ስናይ ደግሞ፣ በደርግ ውስጥ ባንድ በኩል ጥቂት ሃቀኛ ተራማጆች፣ ለሰፊው ህዝብ ጥቅም በርግጥ እስከመጨረሻው ለመሰየት የተነሱ አሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ትምክህተኞች፣ በርግጥም የንኡስ ከበርቴውን ፈላጭ ቀራጭነት ብቻ በሰፊው ህዝብ ላይ አስፍረው ለመኖር የሚፈልጉ፣ እስከመጨረሻው ድረስ የማይለወጡ አድሃሪያች አሉ፡፡አንዱ ያንዱን አንዱ የሌላውን ክንፍ አቋም የሚደግፉ፣ ባጠቃላይ ግን ለሰፊው ህዝብ የሚጠቅሙ እርምጃያችን የማይቃወሙ፣ በመደብ ምንጫቸውም ቢሆን ከሰርቶ አደሩና ከአርሶ አደሩ ጋር በይበልጥ የሚቀራረቡ ህዝባውያንም/ፖፑሊስቶች/ በብዛት ይገኛሉ፡፡በመጀመሪያያች በሁለቱ ክንፎች መካከል ያለው ትግል ገና አልለየለትም፡፡

በዲሞክራሲያም ውስጥ ብዙ ሃቀኛ፣ የሬቮሉሽን ፍላጎት ያላቸው፣ በርግጥ በወዝአደሩ ርእዮተ አለም ተመርተው እስከመጨረሻው ለመታገል የቀረጡ ባንድ በኩል እና እራሳቸው ተወናብደው ሌላውን የሚያወናብዱ፣ ሬቮሉሽኑን ባቋራጭ ለማምጣት የሚቻል የሚመስላቸው፣ የመንግስትን ስልጣን ህዝቡ እራሱ ተደራጅቶና ታግሎ እንዲይዝ ሳይሆን እነርሱ እንዲይዙለት የሚመኙ አድሃሪያች በሌላ በኩል አሉ፡፡ከነዚህ ለመጀመሪያያች የምንለው፣ የሌኒንን ምክር በመከተል፣ የጠባጭን ሁኔታ ጠባጭ ትንተና እናድርግ ነው፡፡የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ሁኔታ በመፈክሮችና በግል ፍላጎት በማሰብ ፈንታ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ካጤንነው፣ የውስጥና የውጭ ሃይሎችን አሰላለፍ በሃቅ ከተመለከትነው፣ ከኢትዮጵያ ፊውዳላዊ ስርአት በተወረሰው የሃሜትና የስም ማጥፋት ዘዴ በመጠቀም ፈንታ ዲሞክራሲያዊና አብዮታዊ ክርክር ካደረግን የማንግባባበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ስለዚህም፣ ክርክሩ ይቀጥል፤ አወናባጅ አስተሳሰቦችና ግምቶች ይወገዱ፣ የጠራና ጠባጭ የፖለቲካ መስመር ይኑር፡፡

ሃቀኛ ውይይት ሲጀመርና ትክክለኛ መስመር ሲሰምር የሚቻለውም ተራማጆች በሙሉ ሃይል፡— ለዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፣ በየወህኒቤቱ ለተወረወሩት ተራማጆች፣ የሰራተኛ ማህበር መሪያች፣ የገበሬ ማህበራት መሪያች መፈታት ሲታገሉ ነው፡፡

አቀማችን የተወሰነ በመሆኑ ብዙ ቅጂያችን አላሰራጨንምና በይዘቱ የምትስማሙ አንባብያን በሙሉ አንብባችሁ ላላነበቡ ብታስተላልፉ፣ ከተቻለም ጋዜጣው የሚበራከትበትን ዘዴ በየፊናችሁ ብትፈልጉ ለትግላችን ይበጃል፡፡